Amhara Professionals Union– አምባ
info@ambapu.org
www.ambapu.org

# አዲስ አበባ (በረራ)ን በተመለከተ ከአማራ ባለሙያዎች ማህበር (አምባ) የተሰጠ የአቋም መግለጫ!
# (መስከረም 2011)

**አዲስ አበባ (በረራ)ን አስመልክቶ የኦሮሞ ፌደራሊስት ኮንግረስ፣ የኦሮሞ ነጻ አውጭ ግንባርና የተባበሩት ኦነግ ያወጡትን የአቋም መግለጫ በጽኑ እናወግዛለን!**

**በአቶ በቀለ ገርባ የተመራው የድርጅቶቹ ተወካዮች የገለጹት አቋም የህግና የታሪክ መሰረት የሌለው ብቻ ሳይሆን የሕዝብ አብሮ መኖርን የሚያፋልስ እና በአንድ አገር ውስጥ አንደኛና ሁለተኛ ዜጋ እንዲኖር መንገድ የሚጠርግ ነው።**

**መግቢያ**

በቅድሚያ በነገድ መለያቸው ምክንያት በቡራዩና በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የአካል መጉደልና የህይወት መጥፋት ለደረሰባቸው ወገኖቻችን ጥልቅ ሀዘናችንን እንገልጻለን።

የነአቶ በቀለ መግለጫ ብዙ አወዛጋቢ ነገሮችን ያካተተ ቢሆንም በተለይ አዲስ አበባ (በረራ)ን በሚመለከት የተንጸባረቀው ሀሳብ ትኩረታችንን ስቧል። ባጠቃላይ በአቶ በቀለ ገርባ የተመራው የአምስት የኦሮሞ ድርጅት ተወካዮች ያሳዩት አቋም ዜጎችን የሚያቃቅር፣ ለግጭት የሚያነሳሳና ህዝብን ስጋት ውስጥ የሚከት ከመሆኑም በላይ የአንድን አገር ዜጎች በአንደኛና ሁለተኛ ዜግነት የሚከፋፈል ሆኖ አግኝተነዋል። በተለይ የሰላም የይቅርታና የህግ የበላይነት የሚሰፍነባት ኢትዮጵያን እየገነባን ነው፤ በለውጥ ጉዞ ላይ ነን፤ ዜጎች ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰው የመስራት መብታቸው መጠበቅ አለበት እየተባለ ባለበት በዚህ ጊዜ አንዱን የሀገራችንን ክፍል የኔ ብቻ ነው ብሎ ማወጅ ጦርነት ከማወጅ አይተናነስም።

በሰለጠነው በ21ኛው ምእተ አመት ከተወለዱበት አገር ውጭ በስደት በተለያዩ አለማት የሚኖሩ የአለም ዜጎች ለመኖሪያ በመረጡት አገር መጤ ሳይባሉ እንደ አገሩ ተወላጅ እኩል መብታቸው ተከብሮ ቋሚ ሀብትና ንብረት አፍርተው በሙሉ ነጻነት ያለ ስጋት በሚኖሩበት ዘመን አያት ቅድመ አያቶቻቸው ህይወታቸውን ሰውተው አጥንትና ደማቸውን ከስክሰው ባቀኑትና ባቆዩት አገራቸው ከዛሬ ጀምሮ ይህ የኔ ብቻ ነው፤ አንተ መጤ ነህ፤ እኔ እስከፈቀድኩልህ ብቻ ልትኖር ትችላለህ የሚለው አባባል ዘመኑን የማይመጥን ኋላቀር ብቻ ሳይሆን በትልቁ ነገደኝነት የተጠናወተው ሆኖ አግኝተነዋል።

ነገዶች ባንድ ዘመን የሰፈሩበትን መሬት የራሳቸው ብቻ አድርገው መቁጠር የዜጎችን እንቅስቃሴ ከመገደቡም በላይ በይገባኛል ጥያቄ ለማያባራ ግጭት የሚዳርግ ነው።

ኢትዮጵያ ለዘመናት ነጻነቷትን ጠብቃ እንድትኖር በተለያየ ጊዜ በውጭ ጠላቶች የተቃጣባትን ጥቃት ዜጎቿ በጋራ መክተው፣ አገር ገንብተው አስረክበውናል። በመሆኑም ማንኛውም የኢትዮጵያ ክፍል የኢትዮጵያውያን የአባቶቻቸው እርስትና የደም ውጤት በመሆኑ ማንም ተነስቶ የኔ ነው የሚልበት የዓለም አቀፍ ህግም ሆነ የሞራል መሰረት ሊኖረው አይችልም።
የአዲስ አበባ (በረራ) ጉዳይም ከላይ ከተጠቀሰው የተለየ አይደለም። አዲስ አበባ (በረራ) ብቻ ሳይሆን አሁን "ኦሮሚያ" የሚባለው "ክልልም" የሁሉም ኢትዮጵያውያን መሆኑን ለነ አቶ በቀለ ለማስታወስ እንወዳለን። አዲስ አበባ (በረራ) ኢትዮጵያውያን ተባብረው ያሳደጓትና ያለሟት ከተማ በመሆኗ ማንም በብቸኛ ባለቤትነት ሊቆጣጠራት የማይችል የኢትዮጵያዊያውን ከተማ ናት። አዲስ አበባ ከኢትዮጵያውያን በተጨማሪም የአፍሪካውያንም ከተማ ሆናለች።

የአማራ ባለሙያዎች ማኅበር (አምባ) ኢትዮጵያውያን በአገራቸው ላይ ስላላቸው መብት ያለው አቋም ከላይ የገለጽነው ሆኖ፣ እነ አቶ በቀለ ገርባ አዲስ አበባ (በረራ) በታሪክም በህግም የኦሮሞ ብቻ ናት የሚል መከራከሪያ ስላነሱ፣ መግለጫው ከታሪካዊ ሁነቶች ጋር ቅርበት አለው ወይ የሚለዉን ለማየት ብቻ የአዲስ አባባ (በራራ)ን ታሪክ አጠር አድርገን በሚቀጥለው ክፍል ለማሳየት እንሞክራለን። አንደኛው በነ አቶ በቀለ የቀረበው ክህደት አዲስ አበባ (በረራ) የምትገኝበት ስፍራ የጥንት የኤካ፣ የጉለሌና የገላን ጎሳዎች መኖሪያና የግጦሽ ቦታ የነበረ ቢሆንም ጎሳዎቹ በሀይል እንዲጠፉ ተደርገዋል የሚለው ነው። ይህ የተጋለጠ ቅጥፈት ነው። እቴጌ ጣይቱ አዲስ አበባን ዳግም ሲመሰርቱም ሆነ ከተማዋ ስትስፋፋ በአካባቢው ይኖሩ የነበሩ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ወይንም ጎሳዎች እነ አቶ በቀለ የጠቀሷቸውን ጨምሮ ከከተማው ጋር አብሮ ከማደግና ከተሜ ከመሆን ያለፈ የማፈናቀል ስራ እንደተሰራ ምንም የታሪክ ማስራጃ ካለመኖሩም በላይ እነ አቶ በቀለ የጠቀሷቸው ጎሳወች የልጅ ልጆች አሁን ድረስ በቦታው ከተሜ ሆነው ይኖራሉ።

በነ አቶ በቀለ መለኪያ አንድ ቦታ ቀድሞ ይኖር ለነበረበት ጎሳ ይሰጥ ከተባለ የተጠቀሱት የኦሮሞ ጎሳዎች ከመስፈራቸው በፊት ማን ይኖር ነበር? አገሩ በኢማም አህመድ (በተለምዶ አህመድ ግራኝ) ጥቃት ከመጥፋቱ በፊትና በኦሮሞ ጎሳዎች በሀይል ከመወሰዱ በፊት ይኖሩ የነበሩት እነማን ናቸው የሚለውን መጠየቅ አስፈላጊ ነው። በማያጠራጥር አኳኋን እንደተረጋገጠው አዲስ አበባ በራራና ወረብ አውራጃ በሚባል የሚታወቀ፣ በቀድሞው ሸዋ ክፍለ ሀገርና አዋሳኙ ይኖሩ የነበሩት የአማራ፣ የጋፋትና የጉራጌ ነገዶች ናቸው። ጨኸቴን ቀሙኝ ካልሆነ በስተቀር በሀይል እንዲጠፉና የጥንት እርስታቸውን እንዲለቅቁ የተደርጉት የኦሮሞ ጎሳዎች ሳይሆኑ የአማራ፣ የጋፋትና የጉራጌ ነገዶች ናቸው። በመሆኑም ታሪክንና ጥንታዊ ባለቤትነትን መሰራት ካደረግን በማያጠራጥር ሁኔታ ባለቤትነቱ የአማራና የጉራጌ ነው።የአዲስ አበባ (በረራ) አጭር ታሪክ በሚቀጥለው ክፍል ቀርቧል።

## የአዲስ አበባ (በረራ) ባለቤትነት ከታሪክ አንጻር

**የአሁኗ አዲስ አበባ፣ የትናንቷ በረራ የዛሬ መቶ አመት አልተመሰረተችም። ነገር ግን ታሪክን ከመቶ ዓመት ወዲህ የመጀመር አባዜ የተጠናወታቸው አካላት የኛ የግላችን ብቻ ናት የሚል የታሪካዊም ሆነ የህጋዊነት መሰረት የሌለው ዘመኑን የማይመጥን ቅዥት ሲቃዡ የታያል። የዛሬዋ አዲስ አበባ ከ600 መቶ አመት በላይ ታሪክ ያላት ሲሆን በ15ኛውና በ16ኛው ክፍለዘመን በወቅቱ በሰሎሞናዊው ሥርወ መንግስት በማእከላዊ መንግስት ዋና ከተማነት  ያገለገለች ጥንታዊ ከተማ ናት። በረራ የነገስታቱ ዋና መቀመጫ በመሆን ከአጼ ዳዊት ቀዳማዊ (1380-1413) ጀምሮ እስከ አጼ ልብነ ድንግል (1508-1540) ከመቶ ዓመት በላይ አገልግላለች። በረራ ወረብ በሚባል አውራጃ ስር ትተዳደር ነበር። በበረራ እና አካባቢው የአማራ፣ የጋፋት እና የተለያዩ የጉራጌ ቋንቋ ተናጋሪዎች ይኖሩ እንደነበር የታሪክ መዛግብት ያሳያሉ። አዲስ አበባ-በረራና አካባቢዋ ከኦሮሞ ፍልሰት በፊት የነበሩ ስልጣኔዎችን የሚያሳዩና በቁፋሮ የተገኙ የጥንታዊ ስልጣኔ አስረጅ ቅርሶችን የያዘ ምድር ነው።**

**“አዲስ አበባ ከታሪክ አግባብ የኦሮሞ ናት” የሚለው የፖለቲካ ድርጅቶች መግለጫ “ከመቸ ጊዜ ጀምሮ ባለው ታሪክ?” የሚል ጥያቄን እንድናነሳ ያስገድደናል። በቅጽል ስሙ አረብ ፈቂህ በመባል የሚታወቀው የአህመድ ግራኝ የጦርነት ዉሎ ጸሀፊ የበረራንና ወረብ አውራጃ ደማቅ ስልጣኔ በዝርዝር ጽፏል። አጼ ልብነ ድንግል በግራኝ አህመድ ሽንብራ ኩሬ (ያሁኒቱ ሞጆ ከተማ) ላይ ድል መሆኑን ተከትሎ ወደሰሜን ያቀኑት የግራኝ ወታደሮች በመንገድ ያገኙትን ስልጣኔ በሙሉ እያወደሙ እንደሄዱ በዝርዝር ጽፏል። ከ1529-1540 ዓ.ም ድረስ ከግራኝ ጋር የተደረገው ወረራ ማዕከላዊ መንግስቱን እጅጉን ስላዳከመው ለኦሮሞ ከደቡብ ወደ ሰሜን ለመስፋፋት ምቹ ሁኔታን ፈጥሮለታል። በዚህ ሂደት ሽምብራ ኩሬ፣ ዝቋላ በረራና መሰል ቦታዎች በኦሮሞ እጅ ሊወድቁ ችለዋል።  አጼ ምኒልክ ወደ ወጨጫም ሆነ ወደ እንጦጦ የሄዱበት ምክንያት የአጼ ዳዊትን ከተማ በረራን ፍለጋ ነው። አጼ ሚኒሊክ የጥንቷን የአጼ ዳዊት ከተማ ቦታ ለማግኘት ያደረጉትን ጥረትና ለምን ወደ ወጨጫ እንደሄዱ በአጼምኒልክ ዜና መዋል ጸሀፌ ትእዛዝ ገብረ ስላሴ “ታሪከ ዘ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ” በተባለው መጽሃፋቸው ከገጽ (95 -96) በሚከተለው መልኩ ጽፈውታል።**

> “ይህ ሁሉ ነገር ከተፈጸመ በሁዋላ ከተማ ለመስራት ወደ አንኮበር ወረዱ ሰራዊቱን በበጋዝ ወደ ኦሮሞ አዝምተዉ የንጦጦ ከተማ ስራ ተጀመረ። የንጦጦ ከተማ ስራ የተጀመረበት ምክኒያት ምንድር ነው ቢሉ አንድ መነኩሴ ኟይ ከደሴቱ ገብቶ ብዙ መጽሀፍት አገኙ። ከዚያም ትልልቅ መጻሕፍት ማውጣት የማይሆንለት ሲሆን አንድ ታናሽ ክብረ ነገስት የአጼ ልብነድንግል የነገረ ራእይ ያለበት ይዞ ወጣ።ይህንንም መጽሀፍ ንጉሱ ባዩት ጊዜ ከአጼ ዮሀንስም ተራርቀው አንድ ልብ ሁነው መግዛታቸውን እንጦጦ ከተማ ሆኖ እግዘትነ ማሪያምን ቅዱስ ራጉኤልን ተክለው  ኦሮሞ የያዘውን አገራቸውን ሁሉ ማቅናታቸውን ራጉኤል መላክ ለአጼ ልብነድንግል በራይ ከነገራቸው ታሪክ ውስጥ አገኙት። ደግሞም ሌላ ብዙ ነገር ተገኘበት። ይሄውም ከድርሳነ ራጉኤል ይገኛል። ነገር ግን የአጼ ዳዊት ከተማ የነበረው የቀድሞው አልተገኘምና ይህ እስኪመረመር በወጨጫ ጋራ በፉሪ ቀኝ ከመካከል ከፍ ያለ ለከተማ የሚመች ስፍራ አይተው ማሰራት ጀመሩ”

**ከገጽ (100 – 101) ባለው ደግሞ የአጼ ዳዊት ከተማ ፍርስራሽ እንጦጦ ተራራ እንደተገኘ በሚከተለው መልኩ ጸሀፌ ትእዛዝ ገብረ ስላሴ በሚከተለው መልኩ ገልጸውታል።**

> “ስሉልታም ሰፍረው ሳሉ የቀድሞው የአጼ ዳዊት ከተማ ፍራሹ ተገኘ ብለው ለንጉሱ ነገሩ። ንጉሱም ወጥተው አዩት። ይህችም ቦታ ራጉኤል መልአኩ ለአጼ ልብነድንግል ራእይ እንደነገራቸው አራዊት ሰልጥኖባት ዳዋ በቅሎባት አገኟት። የቀድሞውም የከተማይቱ ምልክት የኖራው ቅርጽ ግሩም ስራ ሁሉ ተገኘ። በዚህም ጊዜ ንጉሱም ምልክቱን ሁሉ አይተው እጅግ ደስ አላቸው። የአፄ ዳዊት ከተማ የነበረውን እውነተኛውን እንጦጦን ከተማ ታገኘነው የእግዚአብሄር ፈቃዱ ቢሆን ነው። ይህንን ከተማ በኛ ጊዜ የገለጠውን መስራት ይገባናል ብለው ስራው ተጀመረ”፡

የሸዋ መኳንንትም ሆነ አጼ ምኒልክ ወደ እናርያ (የዛሬው ኢሉባቦር)፣ ወደ አሮጌው ዳሞት (የዛሬው ወለጋ) እና ጋፋት የዘመቱት አዲስ አገር ለማቅናት አይደለም። ባለ አገሮቹ የጋፋት ዘሮች እና አማሮች ቋንቋቸው ተወልዶ ያደገበትን እና ለብዙ ሺህ አመታት የኖሩበትን አጽመ ርስታቸውን እንደ አዲስ አገር የሚያዩበት ምንም ምክንያት የላቸውም። ከታሪክ አግባብ ለየአዲስ አበባ (በረራ) ባለቤቷ የአማራ፣ የጉራጌና የጠፋው የጋፋት ህዝብ ነው።

የአዲስ አበባ በረራን ዝርዝር ታሪክ ለመመልከት ይህን መሰናስል ይከተሉ፥ https://tinyurl.com/ya3ryxv7

## አዲስ አበባ አሁን ካለው “ህገ መንግስት” አንጻር

አሁን ያለው የኢፌዴሪ “ህገ መንግስት” የአማራ ህዝብ ባልተወከለበት የትግራይ ህዝብ ነጻ አውጪ ግንባር (ትህነግ) ከኦሮሞ ነጻ አውጪ ግንባር (ኦነግ) እና በወቅቱ ከነበሩ አጋሮቹ ጋር ሆኖ ያረቀቀው ሰነድ በመሆኑና የዜጎችን በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የዜግነት መብት የሚገፍ በመሆኑ የአማራ ባለሙያዎች ማህበር ሁሉን ባሳተፈ መልኩ መሻሻል ወይም በአዲስ ህገ መንግስት መለወጥ አለበት ብሎ ያምናል። ሆኖም ግን አገራችን ባለፉት 24 ዓመታት (የሽግግር መንግስቱን ሳይጨምር) ስትተዳደር የኖረችበት “ህግ” ነውና በዚህ “ህገ መንግስት” ስለ አዲስ አበባ በአንቀጽ 49 ላይ የሚከተለው ሰፍሯል።

፩. የፌደራሉ መንግስት ርዕሰ ከተማ አዲስ አበባ ነው።
፪. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ራሱን በራሱ የማስተዳደር ሙሉ ሥልጣን ይኖረዋል። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።
፫. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተጠሪነቱ ለፌደራሉ መንግስት ይሆናል።
፬. የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በዚህ ህገ መንግስት በተደነገገው መሰረት በፌደራሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይወከላሉ።
፭. የኦሮምያ ክልል የአገልግሎት አቅርቦት ወይም የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች በተመለከተ እንዲሁምአዲስ አበባ በኦሮምያ ክልል መሀል የሚገኝ በመሆኑ የሚነሱ ሁለቱን የሚያስተሳስሩ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ያለው ልዩ ጥቅም ይጠበቅለታል።”

በመሆኑም በዚህ “ህገ መንግስት” መሰረትም አዲስ አበባ ለኦሮሞ እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ህዝብ የፌደራል ዋና ከተማ ከመሆኗ ውጭ የተለየ ባለቤትነትን አይደነግግም። ስለሆነም “አዲስ አበባ በህግ አግባብ የኦሮሞ ህዝብ ናት” የሚለው የፖለቲካ ድርጅቶቹ የብቸኛ ባለቤትነት አቋም “ህገ መንግስታዊ” መሰረት የሌለው ነው።

## የብሔር ፌደራሊዝም አዋጪነት (The Sustainability of Ethnic Federalism)

ምንም እንኳን የተነሳነው አዲስ አበባ የሁሉም ኢትዮጵያውያን እንጂ የአንድ ነገድ አለመሆኗን ለማስመር ቢሆንም የእነ አቶ በቀለ አዲስ አበባ የኛ ነገድ ሀብት ነች የሚለው ተረት ተረት ከሌላ መሰረታዊ ቅዠት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ትንሽ ጊዜ አጥፍተን እናብራራለን::

የእነ አቶ በቀለ መግለጫ ካነሳቸው ነጥቦች የመጨረሻው ይህ "ህገ-መንግስት" ምን ያህል እስካሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ችግሮችን አንደፈታ እና ሌሎች ሀገሮችም ይህን የመሰለ "ህገ-መንግስትን" አንደሚከተሉ ብቻ ሳይሆን ምንም ችግር እንደሌለባቸው ጽፈዋል::

ይህ ማጠቃለያቸው በትንሹ የሚከተሉት መሰረታዊ ችግሮች አሉበት:-

፩. መግለጫውን ያወጡት ፓርቲዎች "ህገመንግስቱ" ምን ያህል በትክክል እንዳልተተረጎመ ለረዥም አመታት ሲነግሩን ቆይተው ነበር (አንዳንዶቹ መግለጫ አውጭዎች ይህን "ህገመንግስት" ለእሱ ብቻ በሚጠቅመው ሁኔታ በሚተረጉመው የትህነግ መንግስት ትእዛዝ ታስረው እስረኞች የነበሩ ናቸው::) አሁን መቶ በመቶ ተገልብጠው ይህ "ህገመንግስት" በትክክል ተተርጉሟል፤ ለዚህም ነው ካለምንም ችግር ኢትዮጵያ አሁንም አንድ ሆና ያለቸው ሊሉን ይፈልጋሉ:: እውነታው ግን ትህነግ አምባገነን ስለነበረ "ህገመንግስቱን" ይተረጉም የነበረው እሱን በሚጠቅመው አኳኋን ስለሆነ ኢትዮጵያን መበታተን ለዝርፊያ ስለማያመቸው ኢትዮጵያ አንዳትበታተን በአምባገነንንቱ አስቁሟል:: ይህ ማለት ግን በዘረኝነት የሰከረውን "ህገመንግስት" ትህነግ ለአምባገነንነት እና ለዝርፊያው አስከጠቀመው ድረስ አልተጠቀመበትም ማለት አየደለም:: የዛሬ አመት ከ700ሺህ ያላነሱ ኦሮሞዎች ከሶማሊያ ክልል የተባረሩት "ህገመንገስቱ" ሰለፈቀደ ነው:: አማራ ከጉራ ፈርዳ እስከ ቤኒ ሻንጉል "ክልል" እንደ ውሻ የሚባረረው እና የሚገደለው "ህገመንግስቱ" ስለፈቀደ ነው:: ስለዚህ "ህገመንግስቱ" ምንም ኢትዮጵያን ከመበታትን ለማስቆም አልረዳም:: ይልቅስ የትህነግ የቀን ጅብ ዘራፊነት ነው ኢትዮጵያን ከመፈራረስ ያዳናት። ይህ ትህነግ ኢትዮጵያን ጠቅሟል ለማለት ሳይሆን ኢትዮጵያ አንደ ሀገር ያለችው "ህገ-መንግስቱ" ስለጠቀመ ሳይሆን ትህነግ መዝረፍ የፈለገው አንድ ኢትዮጵያን በአንድ ላይ ስለሆነ ነው ለማለት ነው::

፪. የመግለጫው አውጪዎቹ የ"ብሔር ፌደራሊዝም" ምን ያህል በሽታ አንደሆነ ባያምኑበትም

አስተዋይነት ስለሚጎድላቸው መጥፎነቱን የሚያረጋገጥ ሃቅ አስቀምጠዋል:: ይህም "ምንም እንኳን አዲስ አበባ የኦሮሞ ብትሆንም ሌሎቻችሁም እንድትኖሩ ፈቅደንላችኋለን" የሚለው ነው:: ሁለት ትርጉም አለው። የመጀመሪያው “ሃሳባችንን ለውጠን የአይን ብሌናችሁን አልወደድነውም ብለን ማባረር በማንኛውም ጊዜ እንችላለን” ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ “እኛን ኦሮሞዎችን ከ"ኦሮሞ ክልል" ውጭ ካሉ "ክልሎች" ብታባርሩን መብታችሁ ነው” የሚል ነው:: ለዚህም ነው ባለፈው አመት 700ሺ ኦሮሞዎች ከ"ሶማሌ ክልል" ሲባረሩ መግለጫ ካወጡት ድርጅቶች አንዱም አነዚህ ኦሮሞዎች ከተባረሩበት ከ "ሶማሌ ክልል" ይመለሱ ብለው ጥያቄ ያላቀረቡት:: እንዴት ነው ይህን የሚፈቅድ "ህገመንግስት" ለኢትዮጵያ ህዝብ ተባብሮ መኖር መሰረት የሚሆነው?

፫. እነ አቶ በቀለ ገርባ የኢትዮጵያ አይነት "ህገመንግስት" ብዙ አገሮች እንዳላቸው እና ምንም ችግር እንዳልፈጠረባቸው በመግለጫቸው ገልጸውልናል:: እነ አቶ በቀለ ይህን ፈጠራ በምን መረጃ ለመደገፍ አንደሚሞክሩ ባናውቅም አኛ ባለን መረጃ የ "ብሄር ፌደራሊዝም" በደቡብ ሱዳን ፣ በኔፓል ፣ በዮጎዝላቪይ አና በፓኪስታን ብቻ ነው ለመተርጎም የተሞከረው እና አየተሞከረ ያለው:: ደቡብ ሱዳን አና ኔፓል በእርስ በርስ ጦርነት እየተናወጡ ሲሆን ዮጎዝላቪያ ከተገነጣጠለች ሃያ አመት ሞላት:: ፓኪስታን እንደቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ኦባማ አስተያየት በጣም ጭንቀት የምትፈጥርባቸው ሃገር ናት ምክንያቱም ፓኪስታን ለመበታተን የቀረበች ሃገር ሆና ነገር ግን ኒኩሊየር ቦምብ አላት:: እነ አቶ በቀለ ገርባ የኢትዮጵያ "ህገመንግስት" ከእነዚህ ሃገሮች አንደሚመሳሰል ነው እየነገሩን ያሉት ። ከዚህ በመነሳት እነዚህ ፓርቲዎች ውስብስብ የ"ብሄር" ጥያቄዎችን መመለስ ሳይሆን መሰረታዊ የማንበብ ችሎታ እንዳላቸው ያጠራጥራል ወይንም ደግሞ ያውቁታል ግን የሚፈልጉት መበታተን እና መጨራረስ ስለሆነ ጉዳያቸው አየደለም።

**መደምደሚያ**

፩. አዲስ አበባ (በረራ) የመላው ኢትዮጵያዊ ናት።

፪. በአቶ በቀለ ገርባ የተመራው የአምስት የኦሮሞ ድርጅት ተወካዮች ያንጸባረቁት አቋም የህዝብ አብሮነትን የሚያቃቅር፣ ለግጭት የሚያነሳሳና ህዝብን ስጋት ውስጥ የሚከት ነው።

፫. አዲስ አበባ (በረራ) በታሪክም በህግም አግባብ የኦሮሞ ብቻ አይደለችም!

፬. ታሪክ ሲመረመር የአዲስ አበባ (በረራ) ቀደምት ባለቤቶች አማራ፣ ጉራጌና የጠፋው ጋፋት ናቸው። የሚያዋጣው ብቸኛ መፍትሄ በእኩልነት በአንድነት መኖር ነው።